EthioLion

# አዩ እማማ

ቲዮዶሬ (ከአቴና)

አዩ እማማ ፣ አዩ እማማ
ምን ትል ይሆን ...
የልጇን ሞት ፣ ስትሰማ ?

ቀኑ ላያልፍ ፣ ሆድ ላይሞላ
መኖር ናፍቋት ፣ ተደላድላ
ኑሮ አንጉቷት ፣ ይሆን ብላ
ቁራሽ ኩርማን ፣ ልትበላ
እርሃብ ችግር ፣ አመልጥ ብላ
ልጇን ቀማት ፣ የሞት ጥላ ።

ሳንቲም ቅርሷን ፣ ሁሉን ቋጥራ
እንጨት ለቅማ ፣ ተበድራ
ልትሰለፍ ፣ ከሰው ተራ
አንድ ልጇን ፣ ላረብ ልካ
ልጄ ብላ ፣ ልትመካ
ምኞት ህልሟን ፣ ልታሳካ
አይ እማማ ፣ ተሳቀቀች
ይብስ መጣ ፣ ቀን ጨለመች
ልጇም ሄደች ፣ ወጣች ቀረች ።

ምነው እማም ፣ በቀረብሽ
ልጅሽ ብትኖር ፣ ከማጀትሽ
ታመሽ ቀና ፣ ብታረግሽ
ምርኩዝ ድጋፍ ፣ ብትሆንሽ
ስትሞቺ ፣ ብትቀብርሽ ።

ቆሎ በልተሽ ፣ ፍርፋሪ
ጦም እንደዋልሽ ፣ ጦም ብታድሪ
ከልጅሽ ጋር ፣ ብትኖሪ
ስትደክሚ ፣ ብትሆን ጧሪ ።

አንቺም ጓጉተሽ ፣ እሷም ጓጉታ
ስትቀርብሽ ፣ ልጅሽ ወጥታ
ስትሆንብሽ ፣ የውሃ ሽታ
አይችለውም ፣ የናት ሆድሽ
መራር ሆነ ፣ ከፋ ሃዘንሽ
ማን ይጋራ ፣ ማን ያግዝሽ
አልቀለለም ፣ ዛሬም ሸክምሽ ።

አዘንኩ እኔ ፣ ላንቺም ለሷም
ኑሮ እያደር ፣ ምን ቢከፋም
ድካም ቢኖር ፣ ምን ቢያለፋም
ተስፋ እንደሆን ፣ ጠፍቶ አይጠፋም
መጽናናቱን ፣ ይስጥሽ ሰላም ።

EthioLion.Com

Ethiopia Will Prevail!